ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ
Forum for Social Studies(FSS)

የፖሊሲ ፍሬ ኃሳቦች

# መሬት አልባነት እና ወጣቶች በኢትዮጵያ

ህዳር 2013 ቁጥር 41

ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ ነክ ምርምሮችን የሚያካሂድ ለትርፍ ያልተቋቋመ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው::

♣ ♣ ♣

የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሠብ ክፍሎችን ኃብዞ ያወያያል::

♣ ♣ ♣

በድረ-ገጹ የሕትመት ውጤቶቹን ዝርዝር ያቀርባል፤ በልማት ዙሪያ ውይይቶችንም ያካሂዳል::

♣ ♣ ♣

በርዕሱ ዙሪያ ኃሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜል አድራሻችን ላኩልን::

♣ ♣ ♣

ኢሜል፡ fss@ethionet.et

ድረ-ገጽ፡ www.fssethiopia.org

## 1. መግቢያ

እንደ ኢትዮጵያ ባሉና የአብዛኛው ነዋሪ መተዳደሪያ አነስተኛ ግብርና በሆኑባቸው ሀገሮች መሬት እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆነ ሀብት ነው። በተለይ ደግሞ በገጠሩ የሀገሪቷ ክፍል ለሚኖሩ ደሀ ገበሬዎች መሬት በጣም አስፈላጊና ብቸኛ የመተዳደሪያ ምንጭ ነው። የህዝብ ቁጥር መጨመር ዋና ምክንያት ቢሆንም የመሬት ክፍፍል፣ ዘገምተኛ የሆነ የገጠር ዕድገት እና የአነስተኛ የመሬት ባለቤትነት በኢትዮጵያ በስፋት የተንሰራፋውን መሬት አልባነት አስከትለዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በርካታና ተፎካካሪ የሆኑ በመሬት ላይ ያሉ ፍላጎቶች በእርሻ መሬት ላይ ያለውን ጫና አባብሰውታል። እነዚህ ፍላጎቶች ሰፋፊ የግብርና ኢንቨስትመንቶች፣ እንደ አበባ እርሻ ያሉ አነስተኛ ግን በከፍተኛ ሁኔታ የሚካሄዱ የንግድ እንቅስቃሴዎች፣እንደ ቢራ ፋብሪካ ያሉ የግብርና ምርቶችን እንደ ጥሬ ዕቃ የሚጠቀሙ ኢንቨስትመንቶች፣የኢንዱስትሪዎች ግንባታና የከተሞች መስፋፋትን ያካትታሉ።በዚህም ሳቢያ የገጠር መሬት ዕጥረትና የመሬት አልባነት ችግር እንዲባባስ ሆኗል። የመሬት ዕጥረትና መሬት አልባነት ችግር በሁሉም የገጠሩን ማህረሰብ ክፍል የሚታይ ቢሆንም ወጣቱ የማህበረሰብ ክፍል በከፍተኛ ሁኔታ የችግሩ ገፈት ቀማሽ ሆኗል። ይህ መሆኑ ዘረፈ ብዙ ችግሮችን ያስከትላል ፤ለምሳሌም ያህል ዝቅተኛ ገቢን፣ የምግብ ዋስትና አለመኖርን፣ለድህነት ተጋላጭነትን ፣ መሬትን ለማግኘት ከፍተኛ የሆነ ፉክክርን፣ስደትን እንዲሁም ችግሩ ሲባባስ የፖለቲካ አለመረጋጋትን ሊያስከትል ይችላል። ይህ የፖሊሲ ምክረ ሀሳብ እ.ኤ.አ በ2016፣2018 እና 2020 በኦሮምያ ክልል እንዲሁም እ.ኤ.አ በ2019 በአማራ ክልል የተሰበሰበ መረጃን መሰረት አድርጎ የተዘጋጀ ምክረ ሀሳብ ነው።የተሰበሰበው መረጃ በዋናነት መሬት እና ወጣቶችን የሚመለከት ሲሆን በተጨማሪ በጉዳዩ ላይ የተሰሩ ጥናቶችም ተዳስሰዋል።

## 2. መሬት የማግኛ መንገዶች

በቀበሌ የተደረገ የመሬት ክፍፍል ፣ውርስ እና ስጦታ አሁን ያሉ ባለመሬቶች መሬት ያገኙባው ሶስቱ ዋና ዋና መሬት የማግኛ መንገዶች ናቸው። የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ መንገዶች ከክልል ክልል ቢለያይም ዋነኛ መሬት የማግኛ መንገዶች ናቸው። እ.ኤ.አ በ2006 በአራቱ ዋና ዋና የግብርና አምራች ቦታዎች የተደረገ ጥናት የሚከተለውን ያሳያል።

| መሬት የማግኛ ዘዴዎች | አማራ | ኦሮምያ | ደቡብ | ትግራይ |
|---|---|---|---|---|
| በቀበሌ ድልድል/ ክፍፍል | 58.8% | 61.5% | 20.6% | 88.4% |
| በውርስ | 39.8% | 35.6% | 73.3% | 10.6% |

ምንጭ፡Teketel and Melsaw (2018 ፤142)

በቀበሌ የተደረገው ክፍፍል የመሬት አዋጅን ተከትሎ በ1967 ዓ.ም “መሬት ላራሹ” የሚል መፈክር (motto) የተጀመረ ሲሆን እስከ ደርግ ውድቀት ድረስ ቆይቷል። በ1989 ዓ.ም (እ.ኤ.አ1997) በአማራ ክልል የተደረገው የመሬት ክፍፍል ከፍተኛ ውዝግብ የነበረበት ነው። በወቅቱ የመሬት ክፍፍሉ ፖለቲካ አንድምታ እንደነበረውና የቀደመው መንግስት ሎሌዎችን የጠቀመ እንደነበረ በአብዛኛው ገበሬ ዘንድ ሲታማ ነበር። ከሰንጠረዡ ማየት እንደሚቻለው ከውርስ በተሻለ በቀበሌ የመሬት ክፍፍል መሬት ያገኙ በከፍተኛ ቁጥር ባሉባቸው ክልሎች መረዳት የሚቻለው ክልሉ የተሻለ የመሬት ባለቤትነት መጠን እንዳለው ፣ የመሬት ድልደላ በቅርብ እንደተካሄደ አልያም በታሳቢ ወራሾች (potential inheritors) ዘንድ አላስፈላጊ ሆኖ በመታየቱ ምክንያት የመሬት ባለቤትነት እንቅስቃሴ ዝቅተኛ መሆኑን ነው። በተቃራኒም እንደ ደቡብ ክልል ባሉ ቦታዎች ከፍተኛ የሆነ የውርስ

መጠኝ እና ዝቅተኛ የሆነ የቀበሌ የመሬት ድልድል ይታያል። ይህ የሚያመለክተው አሳሳቢ የሆነ የመሬት እጥረት መኖሩንና በውርስ ምክንያት የመሬት ይዞታ መጠን በጣም የተበጣጠሰ መሆኑን ነው። ተመሳሳይ የሆኑ ልዩነቶች በአንድ ክልል ውስጥ በሚገኙ ዞኖች ውስጥም ይታያል። ለምሳሌም ያህል በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን በሚገኘው የኩዩ ወረዳ መሬት አልባነት አሳሳቢ ችግር ከመሆኑ የተነሳ በውርስ መሬትን የሚያገኙት ቁጥር አርባ ከመቶ (40%) የሚደርስ ሲሆን በተቃራኒው በአርሲ ዞን በሚገኘው ሊሙ ቢልቢሎ ወረዳ የመሬት አቅርቦቱ የተሻለ በመሆኑ ምክንያት በውርስ መሬትን የሚያገኙት አስራ ስድስት በመቶ (16%) ብቻ ናቸው። አሳሳቢ ችግር በሆነው በመሬት እጥረት ላይ ውርስ የሚጫወተውን ሚና ስንመለከት የሚከተሉትን መረዳት እንችላለን፡-

1. በአሁኑ ጊዜ አብዛኛው መሬት በአረጋውያንና በዕድሜ በገፉ የሕብረተሰብ ክፍሎች እጅ እንደሚገኝ፤

2. ውርስ ወጣቱ የሕብረተሰብ ክፍል መሬትን የሚያገኝበት መንገድ ቢሆንም በሂደቱ ከፍተኛ የሆነ የመሬት መበጣጠስ (fragmentation) ማስከተሉን፤ለምሳሌም ያህል የታሳቢ ወራሾች (potential inheritors) የሚደርሳቸውን የመሬት መጠን ቤተሰቦቻቸው ከያዙት የመሬት መጠን ጋር በሄክታር ሲሰላ በደቡብ ክልል 0.09 ሄክታር ሲሆን በኦሮሚያ ደግሞ 0.14 ሄክታር ነው። ይህ የሚያመለክተው ውርስ ገደብ ካልተበጀለት በቀር ያለውን መሬት በመበጣጠስ (በመከፋፈል) የሚደረገው የማውረስ ሂደት አንዳድ አጥኚዎች እንደሚሉት የጥቂት መሬት ባለቤትነት (micro holding) በማስከተል ወደፊት መከፋፈል የማይችል፤ አሁንም ለግብርና በቂ ያልሆነ መሬትን ያስከትላል።

3. መሬትን በማግኘት ሂደት ውስጥ ውርስ ከፍተኛ ሚና መጫወቱ በተለይም በቤተሰብ አባላት መካከል መሬትን መሰረት ያደረጉ ግጭቶችን ያባብሳል።

በቀበሌ ከሚደረግ የመሬት ድልደላና ውርስ በተጨማሪ የመሬት ስጦታ ሌላው አስፈላጊ መሬትን የማግኛ መንገድ ነው። በአብዛኛው የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ወንድ ልጆች በሚያገቡበት ጊዜ ቢያንስ ለቤት መስሪያ የሚሆን መሬት በስጦታ መስጠት የቆየ ልማድ ነው። ሆኖም ግን ይህ ልማድ በስጦታ የሚገኙ መሬቶችን ህጋዊነት የሚሰጠውና የመሬት ባለቤትነትን የሚያረጋግጠው የ1997 ዓ.ም (እ.ኤ.አ 2005) የመሬት አዋጅ ተከትሎ እየተቀዛቀዘ መጥቷል።ወላጆችም በዚሁ ምክንያት በፊት ለልጆቻቸው በስጦታ የሚሰጡትን መሬት በመተው በመኖሪያ ቀያቸው ልጆቻቸው የመኖሪያ ቤት እንዲሰሩ በመፍቀዳቸው የልጆቻቸው የመሬት ባለቤትነት ጉዳይ አወዛጋቢ ሆኗል።

3. የመሬት አልባነትና በቂ ያልሆነ መሬት ሁኔታ በኢትዮጵያ

በገጠር ለሚኖሩት ኢትዮጵያውያን መሬት አልባነትና[1] በቂ ያልሆነ መሬት እጅግ አሳሳቢ፤ መተዳደሪያቸውን እጅግ እየፈተነ ያለ ጉዳይ ሆኗል። በኢትዮጵያ ያለውን የመሬት አልባነት ሁኔታ የሚያስረዱ አያሌ የጥናት ውጤቶች አሉ። የቀበሌና ወረዳ አስተዳዳሪዎች በቀበሌአቸው/ወረዳቸው ውስጥ የሚገኙ የመሬት አልባ ቤተሰቦች ዝርዝር የላቸውም። በአብዛኞቹ ቀበሌዎች የሚገኙ የነዋሪ ብዛት መረጃ ባለመሬትና ግብር የሚከፍሉ ነዋሪዎችን ብቻ ነው። ይህ ማለት ቀበሌዎች ሙሉ መረጃ ያላቸው ግብር የሚከፍሉ ቤተሰቦችን ብቻ ነው። በኦሮምያ በተደረገ ዳሰሳ ጥናት እንደሚያሳየው የዳሰሳው ጥናት በተደረገባቸው ሶስት ቀበሌዎች ሰላሳ ስምንት ነጥብ ሶስት በመቶ (38.3%) የሚሆኑት የገጠር ቤተሰቦች መሬት አልባ ናቸው። የመሬት ባለቤት ተብለው ከተመዘገቡት ውስጥም ቢሆን ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው መንግስት የመሬት ምዝገባ ለማድረግ ያስፈልጋል ብሎ ካስቀመጠው ዝቅተኛ የመሬት መጠን 0.5 ሄክታር በታች መሬት ያላቸው ናቸው። ከዚህ በታች ያለው ሰንጠረዥ በኦሮሚያና ደቡብ ክልሎች በተመረጡ ወረዳዎች ያሉ የመሬት ይዞታ መጠኖችን ያሳያል።

| | አ ር ሲ ነገሌ | ሻሸመኔ | ወ ን ዶ ገነት | ዳ ሞ ት ሶሬ | አጠቃላይ |
|---|---|---|---|---|---|
| ከ0.5 ሄክታር በታች | 18 | 26 | 71 | 76 | 47.7 |
| ከ1.0 ሄክታር በታች | 45 | 58 | 88 | 95 | 71.5 |
| አሁን ያለ አማካይ የቤተሰብ መጠን | 7.5 | 7.9 | 7.3 | 6.1 | 7.2 |

ከላይ ያለው ሰንጠረዥ በኢትዮጵያ ያለው የመሬት ዕጥረት ምን ይህል አሳሳቢ ችግር እንደሆነ ያሳያል። ከሠባ በመቶ በላይ ቤተሰቦች ከ0.5 ሔክታር በታች መሬት ባላቸው ወረዳዎች መተዳደሪያቸውን በመሬት ላይ ብቻ ማድረግ የማይቻልበት ደረጃ ተደርሷል። የቤተሰብ አባል ቁጥሩ ከፍተኛ በሆነባቸው ቤተሰቦች ችግሩ እጅግ የባሰ ነው።

የመሬት አልባነትና በቂ ያልሆነ መሬት፤ ከፍተኛ የሆነ የቤተሰብ ቁጥር እና አዝጋሚ የሆነ የገጠር ዕድገት ድምር ተፅዕኖ ፖሊሲ አውጪዎችን ሊያነቃና ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጡ ሊያሳስብ ይገባል።

4. መሬት አልባነትና የትውልድ ቅብብሎሽ

መሬት አልባነትን በዋነኝነት ያስከትለው መጨረሻ ከተደረገው የመሬት ድልድል በኋላ የህዝብ ቁጥር

[1] በዚህ የፖሊሲ ምክረ ሀሳብ ላይ መሬት አልባ የገጠር ቤተሰቦች ተብለው የተገለፁት በገጠር ቀበሌዎች የሚኖሩና በመሬት ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት የተደገፈ የመሬት ባለቤትነት መብት የሌላቸውን የገጠር ነዋሪዎች ለመግለፅ ነው።፡

በከፍተኛ ሁኔታ መጨመሩ ነው። በቀድሞው ትውልድ እና አሁን ባለው ትውልድ መካከል ከፍተኛ የሆነ የመሬት አልባነት ልዩነት ይታያል። ለምሳሌም ያህል በኦሮሚያ ክልል ካሉ መሬት አልባ ቤተሰቦች መካከል ሰማንያ ሰባት ነጥብ ሰባት በመቶ ያህሉ የደርግ አገዛዝ ከመውረዱ በፊት በተደረገው የመጨረሻ የመሬት ድልድል ተጠቃሚ ለመሆን ዕድሜአቸው ያልደረሱ ነበሩ። እነዚህ ቤተሰቦች ከ1983 ዓ.ም በኋላ የተመሠረቱ ናቸው። በተመሳሳይ ሁኔታ በአማራ ክልል ከሚገኙ መሬት አልባዎች መካከል ሰማንያ አራት በመቶ ያህሉ መሬት አልባነታቸውን ከህዝብ ቁጥር መጨመር ጋር አያይዘውታል። በደቡብ ክልል ካሉ መሬት አልባዎች ሰባ ሁለት ነጥብ ስድስት በመቶ ያህሉ ዕድሜአቸው ከ20-29 ዓመት ሲሆን፤ሀያ አንድ በመቶ የሚሆኑት ዕድሜአቸው ከ40-59 ዓመት ናቸው። ስድስት በመቶ ያህሉ ብቻ ዕድሜአቸው ከስልሳ ዓመት በላይ ነው።

ለዚህ ችግር መፍትሔ ለመስጠት የተሰጡት አስተዳደራዊ ፖሊሲያዊ ምላሾች ቅራኔ እና ግርታ አላቸው። ለምሳሌም ያህል በአንድ በኩል የመሬት ዕጥረት ችግር ባለበት ሁኔታ የክልል የመሬት አዋጆች የእርሻና እንዲሁም የአርብቶ አደሮች መሬቶች እንዳይከፋፈሉና እንዳይበጣጠሱ ሲያግዱ፤ በሌላ በኩል ግን መሬት የማግኘት መብት የገጠር ነዋሪዎች ህጋዊ መብት እንደሆነ ይደነግጋሉ። ለአብነት ያህል የ1997ቱ የፌዴራል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ (456/1997) በግብርና ስራ ላይ ለሚተዳደሩ አርሶ አደር፣ ከፊል አርብቶ አደር እና አርብቶ አደሮች የገጠር መሬት በነፃ እዲያገኙ ይደረጋል ሲል ይደነግጋል (5፡1፡ሀ) ።

ኢንቨስትመንት እና የመሬት ምርታማነት መቀነስ (መሸርሸር) ከህዝብ ቁጥር መጨመር ቀጥሎ የመሬት ዕጥረትና መሬት አልባትነትን የሚያስከትሉ ጉዳዮች ናቸው። አብዛኞቹ ኢንቨስትመንቶች ለከተማ ቅርብ በሆኑ እና እንደ አዲስ አበባ እና ቢሾፍቱ ከተሞች ላይ ከመሆናቸው ባሻገር ለግብርና ምርት ጥሩ የሆኑ ለም መሬቶችን ወስደዋል።

## 5. የመሬት አልባነት ጉዳቶች

የምግብ ደህንነት አለመኖር፣ መተዳደሪያና ሀብት አልባ መሆን እና ልጆችን ማስተማር አለመቻል የመሬት አልባነት ዋና ዋና ጉዳቶች ናቸው። በኦሮሚያ ክልል የተደረገ የዳሰሳ ጥናት እንደሚያመለክተው ሰማንያ ሰባት በመቶ ያህሉ መሬት አልባ ቤተሰቦች የምግብ ደህንነት የሌላቸው ሲሆን፣ አንድ ሦስተኛው ያህሉ ደግሞ ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት መላክ አልቻሉም። አንድ መሬት አልባ ቤተሰብ ለመኖሪያ ቤት መስሪያ የሚሆን ቁራጭ መሬት እንኳን ማግኘት ሳይችል ሲቀር ችግሩ ጫፍ እንደደረሰ ማሳያ ነው። አሁን ባለው ሁኔታ ሦስት ከመቶ (3%) የሚሆነው መሬት አልባ ህብረተሰብ ጎጆቸውን የሚቀልሱበት ቁራጭ መሬት የላቸውም። ይህ ችግር የመሬት አልባ ቤተሰብ ልጆች በሚያድጉና ዕድሜአቸው ለትዳር በሚደርስበት ጊዜ እየተባባሰ እንደሚሄድ ይጠበቃል። በዚህም እነዚህ ልጆች መሬትን ሳይሆን መሬት አልባነትን ከወላጆቻቸው ይወርሳሉ።

የግጦሽ መሬት እጦት እንዲሁም ለቤት መስሪያ እና ለማገዶ የሚሆን እንጨት ማጣት ተጨማሪ የመሬት አልባነት ችግር ነው። በአንዳንድ ቀበሌዎች እያንዳንዱ የቆመ ዛፍ የግለሰብ ንብረት ሲሆን አንዲት ሄክታር እንኳን የምትሆን የጋራ የግጦሽ መሬት የለም። ይህ በሆነበት ሁኔታ መሬት አልባና ደሀ ቤተሰቦች በምን አይት ችግር ውስጥ እንደሚኖሩ ለመረዳት ከባድ አይሆንም። እነዚህ መሬት አልባ ገበሬዎች ከገጠር ልማት ዕቅዶችና ፕሮግራሞች መገለላቸው ደግሞ ጉዳታቸውን ያባብሰዋል። እንደ መስኖ እና የግብርና ግብዓት አቅርቦት የመሳሰሉ ፕግራሞች መሬት ያላቸው ገበሬዎችን ብቻ ተጠቃሚ ማድረጋቸው መሬት አልባ ገበሬዎችን ያገለሉና ጉዳታቸውን ያባባሱ ሆነዋል።

## 6. መሬት አልባነትን ለመቋቋም መሬት አልባ ገበሬዎች የሚጠቀሟቸው አማራጮች

መሬትአልባና በቂ መሬት የሌላቸው ቤተሰቦች ከችግራቸው ለመውጣት የተለያዩ አማራጮችን ይጠቀማሉ። እነዚህ አማራጮች እንደየቤተሰብ ደረጃ፣ የቤተሰብ ብዛት፣ ዕድሜ እና ፆታ ይለያያል። የቤተሰብ ቁጥራቸው ከፍያለ ቤተሰቦች መሬትን በመከራየት ወይም በጋራ በማረስ ይተዳደራሉ።አሁን ባለው ሁኔታ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት መሬት አልባ ቤተሰቦች ይህንን አማራጭም ይጠቀማሉ። ሆኖም ግን የመሬት ኪራይ ዋጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየናሩ መሄድና እንደ የእኩል ማረስ ያሉ አሰራሮች እየተበላሹ መሄድ ለመሬት አልባውና በቂ መሬት ለሌላው ቤተሰብ አሳሳቢ ችግር ሆኖባቸዋል።ችግራቸውንም ለመቋቋም የቀን ስራ መስራት፣አነስተኛ ንግድ እና ወቅቱን የጠበቀ ስደት (seasonal migration) አማራጭ ያደርጋሉ።

ይሁን እንጂ የአብዛኛው ገጠሩ ማህበረሰብ ዕውቀት፣ ችሎታ እና ልምድ ከእርሻ ጋር የተያያዘ በመሆኑ መሬት መከራየትና የእኩል ማረስ ከሌሎች አማራጮች የበለጠ ተመራጭ የመቋቋሚያ ዘዴ መንገድ ሆኖ ይታያል። የተሻሉት ገበሬዎች መሬታቸውን የሚያከራዩት ለገበያ የሚቀርብ ትርፍ ምርት ለማግኘት ሲሆን፣መሬት ያላቸው የመንግስት ሰራተኞች መሬት የሚያከራዩት ደግሞ መተዳደሪያቸውን ለመደጎም ነው።

የሁሉም አይን በመሬት ላይ መሆኑ በመሬት ኪራይ ዋጋን በእጅጉ እንዲያሻቅብና የመሬት ዕጥረት እንዲባባስ አድርጎታል። የሚገርመው ስራአጥ ወጣቶችና መሬት አልባዎችን ለመደገፍ ተብለው የሚቀረጹ የመንግስት ድጋፎች እንኳ ወጣቱን በማደራጀት በጊዜያዊነት የሚጠቀሙበት ቁራጭ መሬት መስጠት ላይ ያተኮረ ነው።

ትዳር ላልመሰረቱ ከአንደኛ ደረጃ በላይ ትምህርታቸውን ለገፉ ወጣቶች የመሬት ዕጥረት በግብርና ሙያ እንዲተዳደሩ አያበረታታቸውም። እነርሱም ቢሆኑ ግብርናን ኑሯቸውን የሚያሸንፉበትና የሚያሻሽሉበት የመተዳደሪያ አማራጭ አይመለከቱትም። በመሆኑም መሬት አልባነትን ለመቋቋም እንደ የሀገር ውስጥና ከሀገር ውጪ ስደትን ያሉ አማራጮች ሲጠቀሙ ይታያል። በአማራ ክልል ከሚኖሩ መሬት አልባዎች ስልሳ ሁለት በመቶ (62%) ያህሉ የቅርብ ወይም የሩቅ ስደትን እንደ መፍትሔ ይቆጥራሉ። የሀገር

ውስጥ ስደትንም ስንመለከት ከደቡብ ክልል ቀርብ ወይም ሩቅ ከተሞች ከሚሰደዱት ውስጥ ሰባ ዘጠኝ ነጥብ አራት (79.4%) ያህሉ ዕድሜአቸው ከ18-34 የሚሆን ነው።

7. የመፍትሔ ምክረ-ሀሳብ

በሀገሪቱ የሚታየውን የመሬት ችግርና በተለይም የመሬት አልባነት ችግር ለመፍታት የሚከተሉትን ምክረ-ሀሳቦች መሠንዘር ይቻላል፡፡

1. በገጠሪቱ ኢትዮጵያ የሚኖሩ መሬት አልባ ቤተሰቦች እየተጋፈጡ ያሉትን ችግር ለመፍታት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ዘላቂ በሆነ መንገድ ማሻሻል ያስፈልጋል። መሬት ላይ ብቻ በማተኮር የመሬት አልባውን ችግር በዘላቂነት መፍታት አይቻልም።አሁን ባለው ሁኔታ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ቁጥር ላለው መሬትአልባ ዜጋ መሬትን በማቅረብ መፍትሔ መስጠት አትችልም። ያለው የሕዝብ ብዛትና ዕድገት ይህንን ለማድረግ አይፈቅድም፡፡ በመሆኑም በኢኮኖሚው ላይ መዋቅራዊ የሆነ ለውጥ ማድረግ ያሻል። ኢንዱስትሪዎችንና ከተሞችንን ማስፋፋት፤ እንዲሁም የአገልግሎት ዘርፍን ማስፋፋትና መደገፍ በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ላለው ስራአጥ ወጣት ዘላቂ የሥራ ዕድል የሚፈጥር አማራጭ ይሆናል።

2. የቤተሰብ እቅድ በሚመለከት አፋጣኝና አስፈላጊ የሆነ ድጋፍ ያስፈልጋል። አሁን ባለው አብዛኞቹ መሬት አልባ ቤተሰቦች ከፍተኛ የሆነ የቤተሰብ ቁጥር ያላቸው ናቸው። ይህ ሁኔታ አሁን የሚታየውን የመሬት ዕጥረትና መሬት አልባነትን ችግር ስለሚያባብስ መፍትሔ ሊበጅለት ይገባል።

3. የገጠር ልማት ድጋፎች የመሬት አልባ ችግሮችና መሬት አልባነት እያመጣ ያለውን ተፅዕኖዎች ግንዛቤ ውስጥ ሊያስገቡ ይገባል:: የመሬት አልባው የህዝብ ቁጥር ቀላል የማይባልና ከጊዜ ወደ ጊዜም እየጨመረ ያለ ነው:: በመሆኑም የአካባቢ መስተዳድሮች በክልላቸው የሚገኙ መሬት አልባ ቤተሰቦችን ቁጥር በትክክል ሊያውቁ ይገባል:: ይህም እነርሱን የሚያካትት ተገቢ የልማት ዕቅድ ለማቀድ ይረዳቸዋል:: በተጨማሪም የአካባቢ የልማት ዕቅዶች፣ የግብርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ስልጠናዎችና የግብዓት ስርጭት ስርዓቶች መሬት አልባዎችን የሚያካትቱበትን መንገድ ሊያመቻቹ ይገባል::

4. ከሌሎች የልማት ዘርፎች በእርሻ መሬት ላይ ያለውን ጫና ለመቀነስ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ አስፈላጊ ነው:: በዚህ ዕቅድ አለመኖር ሳቢያ የኢንዱስትሪ ዞኖች፣የአበባ እርሻዎች፣ ፋብሪካዎችና የተለያዩ የሥልጠና ተቋማት በእርሻ መሬት ላይ እንዲመሠረቱ ሆነዋል:: ለዚህ አንዱ ማሳያ የሚሆነው በኦሮሚያ ምስራቅ ሸዋ ዞን አድአ ወረዳ የሀገሪቱ ምርጥ ጤፍ የሚመረትበት መሬት ለሌሎች ሴክተሮች መሰጠቱ ነው::

5. መሬት አልባነት በአገሪቷ ካሉ እንደ መስኖ እርሻ አለመስፋፋት፣ የመልካም አስተዳደር እጦት እና የሥራ አጥነት ያሉ መሠረታዊ መዋቅራዊ ችግሮች ጋር የተያያዘ ነው:: እነዚህን ችግሮች ሳይፈቱ የመሬት አልባነትን ችግር መቅረፍ አይቻልም:: መሬት አልባ ቤተሰቦች በአብዛኛው ድሀ ቤተሰቦች በመሆናቸው ሙስናና የህዝብን ችግር ለመፍታት ቅንነት የሚጐድላቸው ባለስልጣናት የመሬት አልባውን ችግር ለመቅረፍ ፈቃደኛ ይሆናሉ ተብሎ አታሰብም::

6. መሬት አልባነት ድህነት እና ተስፋ መቁረጥን ያስከትል:: በኦሮምያ የተደረገ ጥናት እንዳመለከተው አንድ አራተኛ የሚሆነው መሬት አልባ ያለተጨማሪ ዕርዳታና ጥረት ኑሯቸውን ለማግፋት ይቸገራሉ:: በዚህ ሂደት ውስጥ ምርታማ የሆነ መሬትን በኪራይ ማግኘት፤ መጠነኛ የሆነ የቤተሰብ ቁጥር እና ከእርሻ ውጪ ያሉ የሥራ ዕድሎች መኖር ለመሬት አልባ ወሳኝ ጉዳዬች ናቸው:: በተጨማሪም መንግስት ኪራይን በተመለከተ ደንቦችን ሊያለሳልስና በአማራ ክልል እንደተደረገው መሬት አልባውን በተለያየ የገጠር ልማት እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፍና የግብርና ግብዓቶችንም እንዲያኝ ቢደረግ መልካም ውጤት ያስገኛል ተብሎ ይታሰባል::

ፈቃዱ አዱኛ (ዶ/ር)

ምንጭ፡- ፈቃዱ አዱኛ (2013) መሬት አልባነት እና ወጣቶች በኢትዮጵያ


ምስጋናና ማሳሰቢያ

ይህ የፖሊሲ ፍሬ ሀሳብ የታተመው የኦፐን ሶሳይቲ ኢኒሼቲቭ ፎር ኢስተርን አፍሪካ (Open Society Initiative for Eastern Africa) የገንዘብ ድጋፍ ነው በዚህ ህትመት ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የሥራ አመራር ቦርዱን፣የድርጅቱን አጋሮችና የገንዘብ ድጋፍ የሠጠውን የኦፐን ሶሳይቲ ኢኒሼቲቭ ፎር ኢስተርን አፍሪካ (Open Society Initiative for Eastern Africa) አቋምና አመለካከት ላያንጸባርቅ ይችላል::



አድራሻ፡- ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (FSS) ፖ.ሣ.ቁ.፡- 25864 ኮድ 1000 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ፡- 011154 56 05/06 ፋክስ፡- 011154 56 07 ኢሜል፡- fss@ethionet.et ድረ-ገጽ፡- www.fssethiopia.org